አሥርቱ (፲ቱ) ቃላተ አሪት

አሥርቱ ቃላተ አሪት የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ከኪቀ ነቢያት ሙሴ በሲና (ኮሬብ) ተራራ ላይ የሰጠው ነው። አሥርቱ ቃላት፣ አሥርቱ ትእዛዛት አሥርቱ ሕግጋት ዘአሪት ተብለው ይጠራሉ ሁሉም እንድ ነው።

እነዚህ ትእዛዛት ከአባታችን ሙሴ በሁለት ጽላት ተቀርጸው ተሰጡት። በኋላም ሙሴ ኬኰች ሁለት ጽላት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር ቃላቱን በጣቱ ጻፈባቸው። አባታችን ሙሴም ይህን ሕግ በሚቀበልበት ጊዜ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ እንጀራም አልበላ ውኃም አልጠጣ። እግዚአብሔርም በአሥሩ ቃላት ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አድርጓልና አሥሩ የቃል ኪዳን ቃሎች ይላቸዋል።

> "እግዚአብሔርም ሙሴን በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው።" ዘጸ ፴፬፡፳፯ (34፡27)

እነዚህ ፲ቱ ቃላት በሁለት ቦታ ተጽፈው ይገኛሉ። በመጀመሪያ በአሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፪አስከ ፲፯ (20፡2-17) በሁለተኛ ደግሞ በአሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፭፡ ፮-፳፩ (5፡6-21) ነው። ሦስተኛ ደረጃ ማጤን ያለብን ወንድምህን እንደራስህ ውደድ የሚለው የሚገኘው በአሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፲፰ (19፡18) ላይ መሆኑን ነው። እነዚህ ቃላት የተሰጡት በእግዚአብሔር ነው። የተጻፉትም በጽላቱ ላይ ነው። ቦታው ሲና ወይም ኮሬብ ሲሆን ከሕዝቡ ምስክር እንዲሆኑ በአባታችን ሙሴ አማካኝነት ነው።

> "እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ (ዕብነ በረድ) የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው። ዘጸ፡ ፴፩፡፲፰ (31፡18) ዝርዝራቸውም፡-

፩. ኢታምልክ አማልክተ ወኢምንትኒ ዘእንበሌየ፤

፪. ኢትምሐክ ስመ እግዚአብሔር ፈጣሪክ በፈሰስት፤

፫. ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ፤

፬. አክብር አባክ ወእመክ፤

፭. አፍቅር ቢጸክ ከመ ነፍስክ፤

፮. ኢትቅትል፤

፯. ኢትዘሙ፤

፰. ኢትሰርቅ፤

፱. ኢትኩን ሰምዐ በሐሰት በካዕክ ቢጽክ፤

፲. ኢትፍቱ (አትመኝ)፤

ክብር ይግባውና ጌታችን እንደተናገረ አሥርቱ ትእዛዛት በሁለት ከፍል ይጠቀለላሉ። እንደኛ አግዚአብሔርን ለከሚምከክ ሁለተኛ ደግሞ ሰውን ለከመመውደድ ነው። ለከዚህም ጌታ በወንጌሉ እንዲህ አስተማረን።

"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች አርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።" ማቴ.፳፪፡ ፴፯-፵ (22፡37-40)

ሁሉን አንድ አድርገን ሰንመለከተው የአምላካችን ትእዛዙ ፍቅር ነው። ሁሉም ትእዛዛት በፍቅር ተጠቅልለዋል።

"አርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ከማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታል። አታመንዝር አትግደል አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሏል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግምና፤ ለከዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።" ሮሜ.፲፫፡፰-፲ (13፡8-10)

የ፲ቱ ትእዛዛት ዘላለማዊነት፡- አሠርቱ ቃላት ኦሪት

ወይም ትእዛዛት እያልን ስንጠራ ያልገባቸው ስም የኦሪት ነውና አይጠቅምም የሚል አስተሳሰብ ያስባሉ። የኦሪት ሕግ ጸና እንጂ አልተሻረም። ስለዚህም ነገር ሁሉን አዋቂ ሕግን ሰጪ የሆነው ራሱ ባለቤቱ ልዑል እግዚአብሔር በመንጌሉ የነገረን ይህንኑ ነው።

"ኢይመስልክሙ ዘመጻእኩ አስአ ሮሙ ከኦሪት ወከነቢያት ዘእንበለ ጸዕሙ ከመ አፈጽሞሙ"

"እኔ ሕግንና ነቢያትን ከመሻር የመጣሁ አይምስላችሁ ልፈጽም እንጂ ከመሻር አልመጣሁምና" ማቴ.ፍ፡፲፯ (5፡17)

ጌታችንም እንደት ሊፈጽሟቸው ወይም ሊያጸናቸው እንደመጣ በመንጌሉ በዝርዝር ተጽፏል። ዘላለማዊነታቸውም እስከ ፍጻሜ ዘመን በዚህ ምድር እንደሚኖር እንዲህ ይላል።

"እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የመጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም" በዕብራይስጥ የፊደል ገበታና ቁጥር አሥረኛዋ "ዮድ" ትባላለች አጻጻፏም እንደ ነጥብ ነው። ስለዚህም የመጣ ወይም አንዲት ነጥብ ያለው ለዚህ ነው። በምሥጢሩ ደግሞ አሥረኛዋ ትእዛዝ ሊትፍቱ (አትመኝ) ስትሆን ይህችን በአጻጻፍ የፊደል ቁጥር ከሌሎች ማነሷን አይቶና ንቆ ቢያስተምር እግዚአብሔር ከሕይወት መጽሐፍ ይደመስሰዋል በመንግሥተ ሰማያትም ስፍራ የለውም። "ዝኒ ፈትሐ አሐተ እምአላ ትእዛዛት እንተ ተሐፅፅ ወይሜሕር ከመዝ ከሰብእ ሕፁፀ ይከውን በመንግሥተ ሰማያት"

"ከኧቱ ቃላት አንዲቱ ታናሽ ናት ብሎ ከራሱ የሚሠራ ከሌላው የሚያስተምር ከመንግሥተ ሰማያት የመጣ ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህም ፲ቱ ቃላተ ኦሪት ከ ፯ቱ ቃላተ መንጌል ጋር ጸንተው የሚኖሩ ናቸው።

"ታደርጉትም ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን አሥሩን ቃላት
ነገራችሁ በሁለቱም በድንጋይ ጽላት ላይ ጻፋቸው።" ዘዳ፬፡፲፫
(4፡13)

ሰንበት

ሰንበት የሚለው ጥሬ ቃኩ "ሰንበተ" የሚል የግእዝ ግስ ሲሆን ትርጉሙም ሰነበተ፣ አከበረ፣ ቆየ ሰንበት ማለትም የተከበረ የቆየ የሰንበት የዕረፍት ቀን ሰባተኛው ቀን ማለት ነው። ከዚህ በተለየ ግን በሃይማኖታዊ ምስጢር ትንተናው የተባረከ የተቀደሰ የተለየ ቀን ማለት ነው። እግዚአብሔር እምላክ ዘፍጥረትን የሆኑትን የሚይከመው እሠርቱን ትእዛዛት የሰጠን ሲሆን ከእነዚህም አንዱ የሰንበትን ቀን እናከብረው ዘንድ ነው።

የሰንበት አከባበር ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ከሌሎች ሁሉ ልዩ ናት። እንዳንዶች መከበር ያለበት ቅዳሜ ነው ብለው ይናገራሉ ሌሎች ደግሞ ቅዳሜ ተሸራለች መከበር ያለባት እሑድ ናት በማለት ያስተምራሉ። እኛ ግን ኦርቶዶክሳውያን ከራሳችን በማፍለቅና በመፈለሰፍ ሳይሆን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ያዘዘንን በመከተል ሁለቱንም ሰንበት (ቅዳሜና እሑድን) እናከብራለን። ልናውቀው የሚገባ ነገር ግን ከዕለታት ሁሉ እሑድ ትልቃለች ትበልጣለችም። ሁለቱንም ሰንበታት በዝርዝር እንመልከት።

ቅዳሜ

ይህች ዕለት ቀዳሚት ሰንበት ተብላ ትጠራለች። ይህች ቅዳሜ እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ፈጥሮ ያረፈባትና እናከብራት ዘንድ ያዘዛት ቅድስት ዕለት ናት። እግዚአብሔር እምላክ የሠራውን ሥራ በዚህች ቀን ፈጽሚል ማለትም ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐርፏል። "ወባረካ እግዚአብሔር ለዕለት ሳብዕት ወቀደሳ" እግዚአብሔር ሰባተኛይቱን ቀን ባረካት ቀደሳትም" ዘፍ. ፪፡፪ (2፡3)

ስለዚህ እግዚአብሔር የባረከውንና የቀደሰውን እንደገና አይከሠጠሙምና፣ እኛም ዕለቱን በቅድስናው እናከብረዋለን። እናከብረውም ዘንድ ከልዑል እግዚአብሔር

ዘንድ ትእዛዝ አለ እንዲህም ይላል፡-

"ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ" ሰባተኛይቱን ቀን ቅዳሜን አስባት አከብራት ዘጸ. ፳፡፰ (20፡8) ይህ አንግዲህ ከአሥርቱ ትእዛዛት አንዱ ነው። ቅዳሜ ተሸራሪት ብሎ የሚያምን የጌታ ቃሉ አይሻርምና ትእዛዛቱም ዘላለማውያን ናቸው፤ ሊያስተውል፣ ሊያምን ይገባዋል። አለዚያ ቃሉ እንደተናገረ በመንግሥተ ሰማያት ሰፍራ አይኖረውም።

> "እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ እንዲት የሙላ ወይም እንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዱቱን የሚሽር ከሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ሚንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል" የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ሚንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል" ማቴ. ፭፡፲፰-፲፱ (5፡18-19)

እርግጥ አይሁድ ይህችን ቅዳሜ ሰንበትን ሲያከብሩ ከዘረጉ ሳያጥፉ፡ ካጠፉ ሳይዘረጉ፣ ከከፈቱ ሳይዘጉ፡ ከዘጉ ሳይከፍቱ ነው። እኛ ግን በዚህች ቀን መንፈሳዊና በጎ ደጋግ ሥራ እየሠራን ፈጣሪን እያመሰገንን እናከብራታለን፣ እንድንጨነቅበት ሳይሆን ሐሤት እናደርግበት ዘንድ እግዚአብሔር ሰንበትን ሠራልን።

> "ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወእኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት"
>
> ሰንበት ለሰ ለሙ ተፈጠረች እንጂ ለሙ ለሰ ሰንበት አልተፈጠረም። ማር. ፪፡፳፯ (2፡27)

ለዚህ በዚህች ቀን ለሙም እንሰሳም የሚያርፍባት ቀን ሆነች። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሕግ ሁሉ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም። ደግሞ እሱ የፍጥረት ሁሉ ጌታና ከፍጥረቱ ሁሉ የሚያዝን ነውና በዚህች በቅዳሜ ሰንበት እንሰሳት እንኳ ያርፉ ዘንድ አዘዘ። በዚህች ቀን እግዚአብሔር የሥጋ ዕረፍትን ሰጠን ከነፍሳችንም ከብር እንድናመሰግነው ሰንበቱን ጠብቀ ብሎ አዘዘን።

የቅዱሳን አበው የሐዋርያት ቃል በዲድስቅልያ ስካሚ ስምንተኛ (38ኛ) አንቀጽ ስለ ስንበት ሲናገር እንዲህ ይላል። "ወገብረ ከነ መዋዕለ በዓላት ፍሥሐ ከነፍሳቲነ" "ከሰሙነቶቻችን ደስታም የበዓላት ቀኖችን ሠራልን።"

"ሰባተኛው ቀን ግን ከእግዚአብሔር እምካከሀ ሰንበት ነው። አንተ አንደምታርፍ ኰሌሀና ገረድህ ያርፉ ዘንድ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ኰሌሀም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ... ስለዚህ እግዚአብሔር እምካከሀ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ።" ዘዳ. ፭፡ ፲፬-፲፭ (5፡14-15)

ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና በእዱስ ኪዳንም የሚሠራ የሚይከወጥ ሕግ ነው። ከዚህም ነበር ቅዱስ ኩቃስ እንደጻፈው። የጌታ ቤተሰቦች በቅዳሜ ዕለት ሥራ ያልሠሩት። ወደ መቃብሩም ያልሄዱት።

"በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ" ኩቃ. ፳፫፡፶፮ (23፡56)

እሑድ

በስድስት ቀናት ውስጥ የሚታየውንም የማይታየውንም ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎ ቅዳሜን ቀድሶ ለከብሩ ያለ እምካካችን እግዚአብሔር የሰው ልጅችን ከማዳን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣልትን ዕለተ እሑድ የዕለታት በኩር አድርገን እናከብራታለን።

"ኦ ዛቲ ዕለት ቅድስቱ ለለብ ቡርክቱ ለመልድ ልዕልቱ ለመንፈሰ ቅዱስ ንትፈሳሕ ባቲ መንትሐሠይ ባቲ ቀድሰዋ ከመ ትትቀደሱ ባቲ"

"ወዮ ይህች ዕለት እብ የቀደሳተ መልድ የባረካት መንፈሰ ቅዱስ ከፍ ከፍ ያደረጋት ናት በርስዋ ደስ ይበለን በርስዋም ሐሤት እናድርግ ትከብሩባት ዘንድ ለከብሩዋት"

አባታችን ቅዱስ እትናቴዎስ የአሑድ ዕለትን አንዲሀ ከብሯን ከገለጸ ዘኋላ ኬሎቹን ሰድሰቱን ዕለታት በመጥራት ኑ እናከብራት ብሎ የከርሰቲያኖች ሰንበት ብሎ ያመድሳታል።

"የበዓላትን ዘሑር ኑ እናመሰግናት ይሀችሙም የነበረች ሰንበተ ክርሰቲያን ናት"

"ንዑኬ ንመድሳ ከበኩረ (ዕለታት) ዘዓላት አንተ ይእቲ ሰንበተ ክርሰቲያን ቅድስት" የዘጠኙ በዓላተ ትሰብእት በኩር አሑድ ናት"።

አሑድ የሚለው ቃል የግእዝ ሲሆን "አሐደ" አንድ አደረገ ከሚለው ግሥ የመጣ ነው። ይሀች ዕለተ አሑድ ከዕለታትና ከበዓላት ሁሉ የመጀመሪያ ናትና "በኩረ ዕለታት" የበዓላት ሁሉ መጀመሪያ ትባላለች። ይሀች ዕለት ከብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርሰቶስ በመቤአዙ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ከአመቤታችን ለው የሆነላት መልድ ከሥጋ ጋር የተዋሐደባት በከበበ ትሰብእት ዳግም ከፍርድ የሚመጣባት ይሀችው ዕለት ናት። ሞትን ድል አድርጎ የተነሣባት፣ ሲኦልን የመዘበረባት፣ ገነትን የከፈተባት፣ አዳምንና ሔዋንን ከነልጆቻቸው ነፃ ያወጣባት፣ የሞት መውጊያ የጾለጾመባት፣ ከከርሰቲያኖች የድል ቀን ናት ለዘዚህ አሑድ የከርሰቲያን ሰንበት ናትና ቤተከርሰቲያናችን ታከብራታለች። አንዳንድ ሰዎች በዘመነ ቆለጠንጢኖስ ሚከበር የተጀመረ ይመስላቸዋል። በዚያ ዘመን 318ቱ ኪቃውንት ከአባቶቻቸው ነቢያትና ሐዋርያት የመረደውን እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕግ አጸደቁልን አንጂ አዲስ የፈጠሩትና የደነገጉት ምንም አንግዳ ነገር የለም። ከዚህም በመቀጠል የዕለተ አሑድን ከብር በብሉይና በሐዲስ ኪዳን እንመልከት።

<u>አሑድ በብሉይ ኪዳን</u>

አሑድ በብሉይ ኪዳን ዘፍጥረትን ሰንመለከት እግዚአብሔር ፍጥረትን የጀመረባት ዕለት መሆኗን አናገኛለን። ለዘዚህም የላምንቱ የመጀመሪያ ቀን ትባላለች። ዘፍ. ፩፥፭ (1፥5) እትናቴዎስ "ዛቲ ዕለት ቀዳሚዊት ይእቲ ወእኪ ደኃራዊት"

ዮሐ. ፳፥፩ (20፥1)

> "ይህች ዕለት ቀዳሚት (የመጀመሪያ) ናት ደኃራዊት (ኋለኛይቱ) አይደለችም" ይላታል።

ቅድመ ከርሰትና በዘመነ ብሉይ አሑድን እንደት ያከብሯት እንደነበር በኦሪት ዘኁዋሙያን ስንመለከት እግዚአብሔር አስቀድሞ ከድኅነት የሠራት መሆኗን እናገኛለን። ዘኁ. ፳፰፥ ፲፭-፳፩ (23፥15-21)

> ከቁጥር ፲፭-፲፯ "... ከሰንበት ሚግስት ፍጹም ስባት ጊዜ ሰባት ቀን ቁጠሩ እስከ ሰባተኛ ሰንበት ሚግስት ድረስ አምሳ ቀን ቁጠሩ አዲሱን የእህል ቁርባን ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ... "

ይህም ቁጥር ከሚያዝያ አሰራ ሰድስት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ አራት ቀን ነው ይህ ስባት ሱባዔ ይሆናል። አንድ ሱባዔ ሚለት ሰባት ቀን ሲሆን ሰባቱ ሱባዔ አርባ ዘጠኝ ቀናት ይሆናል። አምሳኛው ቀንም አሑድ ላይ ይውላል። ልብ አድርገን ስንመለከት ቁጥሩ የሚጀምረው ከሰንበት ሚግስት ስለሚል ነው። አንደኛው ቀን አሑድ ይሆናል አምሳኛውም ቀን አሑድ ዕለት ላይ ያርፋል። ይህችም ዕለት በዓለ ሠዊት ተብላ ትከብራለች። በዚህች ዕለት ከበኩራት ቁርባን የእህልና የመጠጥ ቁርባን የሚቃጠል የእሳት ቁርባንም እንዲሆን ጠቦቶች ቢጎቹና ወይፈን ከኃጢአት መለዋወጥና ከደኅንነት መለዋወጥ ያቀርባሉ።

> ቁ. ፳፭ "በዚያን ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላችሁ ዘንድ ታውጁላችሁ የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉበት በምትቀመጡበት ሀገር ሁሉ ከልጅ ልጃችሁ የዘላለም ሥርዓት ነው"

በዚህች በዕለተ አሑድ (ስንበት) የሰው ልጆች ሁሉ ድኅነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የታመጀባት የፍጥረት ሁሉ የመዳን ቀን በቃሉ እንደተመለከትነው የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉባት እንደተባለ ይህች ዕለት ዕረፍት ሥጋዊና ዕረፍት መንፈሳዊ ያለባት ናት። በቤተክርስቲያናችን ሕግ መሠረት በዕለተ አሑድ ስንበት ዕረፍት ሥጋዊ የተባለ አርሻ፣

ቁፋሮ፣ ሙጣ ሙሪድ የኬክባት፣ ዕረፍት መንፈሳዊ ጸም፣ ሰግደት፣ የኬክባት ሕመም ድኩም፣ በሽተኛ የሚጐበኝባት፣ ደዌ ካልፀናበት በሰተቀር ፍጥረት ሁኩ በመቅደሱ ከሙዳሴ፣ ከዝማሬ፣ ከቅኔ፣ ከትርጓሜ ከሰባሔ፣ ከቅዳሴ የሚተጋባት ቅድሰት ዕከት ናት።

ከርሰቲያኖች ሆይ በዚህች ዕከት የሰሙ ልጅ ሁኩ ወደ ቤተክርሰቲያን መሄድ እንዳለበት ይህን ቃኩን አዩና እንድትፈጽሙት እግዚአብሔር ይርዳችሁ። "ሰባት ሳምንትም ትቆጥራለህ መከሩን ሚጭድ ከምትጀምርበት ቀን ጀምሮ ሰባት ሳምንት መቁጠር ትጀምራለህ"

> "ሰባት ሳምንትም ትቆጥራለህ፤ መከሩን ሚጨድ ከምትጀምርበት ቀን ጀምሮ ሰባት ሳምንት መቁጠር ትጀምራለህ።አምላክህ እግዚአብሔረ በባረከህ መጠን በፈቃድህ የምታቀርበውን አምጥተህ ከአምላክህ ከእግዚአብሔር የሰባቱ ሱባዔ በዓል ታደርጋለህ። አንተ፣ ወንድ ልጅህና ሴት ልጅህ ወንድ ባሪያህና ሴት ባሪያህ በአገርህም ደጅ ሙሰጥ ያለው ሌዋዊ በመካከልህም ያኩት መጻተኛና ድህ አደግ መበለትም አምላክህ እግዚአብሔር በዚያ ሰመ ይጠራበት ዘንድ በሚመርጠው ሰፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ደሰ ይበላችሁ።" ዘዳግም ፲፮፥፱ - ፲፩ (16፥9 - 11)

በብኩይ ኪዳን አንዲህ ከሆነ ሕግ በጸናባት በሐዲሰ ኪዳን ደግሞ የበለጠ መሆኑን አሰተውኩ።

<u>አሐድ በሐዲስ ኪዳን</u>

ከላይ እንደተመለከትነው አምላካችን እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን የሠራባት የተመረጠች ዕከት (ሰንበት) ዕከተ አሐድ ናት። ከአመቤታችን ከቅድሰት ድንግል ሚርያም የተጸነሰው በዚህች ቅድሰት ዕከት ነው። ሙሰና መቃብርንም ደምሰሶ አጥፍቶ ድል አድርጎ ከሞት የተነሣው በዚህች በዕከተ አሐድ ነው።

> "በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ

> መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ...መልአኩም መልሶ ሴቶቹን እላቸው፡-እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ እውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም።" ማቴ. ፳፰፥፩-፲ (28፥1-10)

በብዙይ ዘመን የተደረገው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን የተፈጸመ ነውና ጌታችን ከብር ይግባውና አሪትን ከመሻር ሳይሆን ልፈጽማት መጣሁ ብሎ በመንጌሉ እንደነገረን ማቴ. ፭፥፲፯ (5፥17) በአሪት ዘኬዋውያንና በዘዳግም ላይ እንደተመለከትነው የእምላካችን ሕግ ከዘላለም የሚጸና ነው ብሎ እንደተናገረ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ከሞት ከተነሣ ከሰባት ሱባኤ በኋላ ሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን የሰጠባት ዓለም ሁሉ መንጌልን የሰማባት ዕለት ይህች የተመረጠች ዕለተ እሑድ ናት።

> "በዓለ ሃምሳው የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም ባንድ ልብ ሆነው እብረው ሳሉ ... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው" የሐዋ. ሥራ ፪ (2)

በዚህች የድኅነት ቀን ከርስቲያኖች እየተሰበሰቡ ከሌሎች ዕለታት በተለየ የምስጋና ቀን ሆነች። ቅዳሴ ይፈጸምባት ትጣኣሙ ይነገርባት ዘንድ ሥርዓት ሆነ። ሥራ ፳፥፯ (20፥7)። ምእመናንም በዕለተ እሑድ ከችግረኞች የሚመጸመተውን ገንዘብ ሁሉ በዚህች ቀን እየሰበሰቡ ምንዱባንን ይረዱበት ነበር። ፩ቆሮ. ፲፮፥፪ (16፥2)። ይህ ሥርዓት ነው ዛሬም በኦርቶዶክስ ቤተ ከርስቲያናችን የሚፈጸመው። የሐዋርያት አባቶቻችን በረከታቸው ይደርብንና ይህችን ዕለተ እሑድ

> የጌታ ቀን ብለው ይጠሩዋታል ራዕይ ፩፥፲ (1፥10)

ከሌላው ዓለም በተለየ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ብቻ ስንበታትን (ቅዳሜንና እሑድን) ታላቅ ከብር በመስጠት ያከብራሉ። የጥንት ከርስቲያኖችም ያደርጉት እንደበረው በቅዳሜና በእሑድ ዕለት ተጠብቀው ከእግዚአብሔር የምስጋና ቀንና ድሆችን ከመጎብኘት

የታመመን ከመጠየቅ በተከያየ መከራ ያለውን በማጽናናት ያሳልፉታል። ሁኑን የሥጋ ሥራቸውን በዕለተ ዐርብ ያጠቃልላሉ። ይህም ምሳሌነቱ ዕለተ አሑድ የከብር ባለቤት ዳግም ከፍርድ የሚመጣባት ቀን ተብላ የምትታመን ናትና ተሰናድቶ መጠበቅን የሚያሳይ የሚገባ ሥራ ነው።

"ወጸልዩ ባሕቱ ከመ ኢይኩን ጉያከሙ በክረምት ወበሰንበት"

"ነገር ግን ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ" ማቴ. ፳፬፥፳ (24፥20)

ሰለዚህ ይህች ቅድስት የሰንበት ዕለት ምእመናን ሁሉ በመቅደሱ በጸሎት የሚተጉባት እንጂ የሚተጉባት እይደለችም።

"ኢይምጻእከሙ ግብተ ወኢይርከብከሙ እንዘ ትነውሙ ወናሁ አብከከሙ ከኩልከሙ ትግሁ።"

"ድንገት እንዳይመጣባችሁ ተኝታችሁም እንዳያገኛችሁ፡ እነሆ ሁላችሁም ትጉ እላችኋለሁ። ማር፡ ፲፫፡፴፮-፴፯ (13፥36፥37)

ከዚህ እምካካዊ ቃል የተነሣ ምእመናን ሁልጊዜ ይልቁንም በሰንበት በቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ይሰበሰባሉ፣ ይጸልያሉ፣ ይቀድሳሉ። እያንዳንዱን ሰንበት ተከፋፍለው በማኅበር ጽዋ ይጠጣሉ "ሰንበቴ" ብለውም ይጠሩታል። ዘዚህ ርዕሰ የተጸፈውን ተመልከቱ።

የጽዋ ማኅበር ሰንበቴ

የጽዋ ማኅበር ሰንበቴ ከርስቲያኖች የሚፈጽሙት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ከርስቲያናዊ ምስክርነት ያለው ታላቅ የቅድስና ትሩፋት ነው። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የተጸፈከት ታላቅ ምሥጢር የሚገለጽበት ዓላማው መንፈሳዊ ሥራውም የጽድቅ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር በረድኤት የሚገኝበት ነው።

> "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው አሆናለሁና" ማቴ ፲፰፡፳ (18፡20)

የጽዋ ማኅበር፡-

ከርስቲያኖች በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ስምች ስም እየተሰበሰቡ በቤተክርስቲያን ወይም በየቤታቸው የሚፈጽሙት የቅድስና ሥራ ነው። ይህም እግዚአብሔር በመካከላቸው እንዳለ በማመን የሚከውኑት የመንፈሳዊ በረከት ነው፤ ይህንንም ከእንድ ከርስቲያን ቤት ወደሌላኛው እያዘዋወሩ ያደርጉታል። መነሻውም አንደኛ በዘመነ ብሉይ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በደጉ አባት አብርሃም ቤት ተገኝቶ ሣራ የሠራችውን ተመግቦ ቤታቸውንም ባርኮ የተዘጋውን በር ከፍቶ የሣራን ማኅፀን ከፍሬ አብቅቶ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በመካእከቱ አድሮ በሎጥ ቤት ተገኝ፡ ሎጥንም ከታላቅ መከራ መካእከቱ አጼን ይዘው አወጡት። ዛሬም ከርስቲያኖች መሶቡንና ጽዋውን በመያዝ በየወሩ በየቤቱ እየተሰበሰቡ ይህንን ያስባሉ፤ (ዘፍ ፲፰ (18) የመሶብ ወርቁና የጽዋው መግባት የእግዚአብሔር መግባት ምሳሌ ነው፡ ምሥጢሩን እንመከከተዋከን። ከአብርሃምና ከሣራ እንዲሁም ከሎጥ የተደረገው የእግዚአብሔርን ቸርነት ጽዋው በገባበት ቤትም ይደረግ ዘንድ የምእመናን ምኞትና ጸሎት ነው።

ሁከተኛ በዘመነ ሐዲስ በወንጌልም ተጽፎ እንደምናገኘው የከብር ከብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ በመዋዕከ

ሥጋዊው በሚያምኑት ቤት አየገባ አየተመገበ ቤታቸውንም ይባርከካቸው ኃጢአታቸውንም ይደመስስላቸው ነበር። ከምሳሌ በቢታንያ ሀገር በሐምጻሙ በስምዖን ቤት (ማቴ ፳፮፡፮ (26፡6) በኢያሪኮ አገር በቀራጩ በዘኬም ቤት (ኩቃ ፲፱፡፩-፲ (19፡1-10) የማርያምና የማርታ ወንድም በሆነው በአልአዛር ቤት (ኩቃ ፲፡፴፰-፵፪ (10፡38-42)

ዛሬም ምእመናን ኃጢአተኞችን የሚይጸየፍ ጌታ በቤታቸው ይገባ ዘንድ መሶባ ወርቁንና ጽዋውን ይዘው ባሉበት ቤት ሁሉ በረከት ይገባበታል።

> "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱ ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።" ራዕ ፫፡፳ (3፡20)

እንዲህ ያለን ጌታ ምእመናን ይህን ምሥጢር በሚገልጽ የጽዋ ማኅበር ይዘክሩታል። ዘለረ የሚለው የግእዝ ቃል አሰበ ማለት ነው። በዚህም ረቂቅ ምሥጢር የሚታሰበው ቀጥሎ ያለው ነው፡፤

<u>መሶበ ወርቅ</u>፡- መሶበ ወርቅ በውስጡ ኅብስት ይደረግበታል የዚህ ምሥጢሩ መሶበወርቅ የእመቤታችን ምሳሌ። መሶቡ የወርቅ መሆኑ የእመቤታችን ንጽሕናን የሚያመለክት ነው። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር ፵፬ቁጥር ፱ (44፡9) እመቤታችንን ንግሥቲቱ ብሎ የወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና በቀኝህ ትቆማለች ብሎ እንደመሰከረው። ከርሰቲያኖች መሶባቸውን አጎናጽፈው ሽፍንፍን አድርገው ይይዙታል፡፤ ምክንያቱም ቅድስት የሆነች እመቤታችን ክብር ይገባታል። በመሶበ ወርቁ ውስጥ የሚደረገው ኅብስት "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" ያለ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። (ዮሐ፡፮፡ ፴፭) ይህንንም አክብሮ መያዝ ብቻ ሳይሆን ይሳለሙታል ይስሙታል ከብሩ ከእግዚአብሔር ነው።

<u>ጽዋ</u>፡- የጽዋውም ምሥጢር አንደ መሶበ ወርቁ አንድ

ነው። ጽዋው የእመቤታችን ምሳሌ ነው። በውስጡ ያለው ወይን ወይም ጸበል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ምሳሌ ነው። ከብር ይግባውና መሶበ ወርቁና ጽዋው የጎበስቱና የጸበሉ መያዣ የእመቤታችን መሆኑ ጌታችን ሥጋንም ደምንም የተዋሐደው ከእርሷ ብቻ ነውና። ምእመናንም ይህን በመረዳት በጽዋ ሚጎበራችን የጌታችን መከራውን በቀራንዮ ያደረገውንም ሞቱን እያሰብን ይህን ደግ ሥራ እናደርጋለን፡፤ ዋና ዓላማው ይህ ሆኖ ሳለ በመሰባሰባችንም የተቸገሩ፣የተራቡ፣ የተጠሙ ነዳያንን እናሰባለን፡፤ ይህም ኪሆን እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ የሥጋ ወደሙንና የጽዋ ሚጎበር መሰባሰብን እንዳሰተማረን ልናደርገው ይገባል።

፩. የእግዚአብሔርን ሚጎበር እንዳንንቅ፡- ሚጎበሩ እግዚአብሔር የሚገኝበት መሆኑን እንድናውቅ። ስለዚህም ነው የእግራችንን ጫማ የምናወልቀው።

፪. በሚጎበራችን ጊዜ ከልክ ያለፈ ድግስ እንዳናደርግ የኬካቸውንም ሰም እንዳናሳፍር።

፫. ከተቸገሩ ከተራቡ እንድናሰብ፤

፬.ከልክ በላይ እንዳንበላና እንዳንጠጣ። በተለይ ስካር ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

ኬሎችም ብዙ መልእክቶች ያስተምረናል። የሥጋ ወደሙን መልእክት ከጽዋ ሚጎበሩ በመለየት ፩ቆሮ ምዕራፍ ፲፩ ከቁጥር ፲፯ ጀምሮ እስከ ፴፬ ያለውን (1ቆሮ 11፡17-34) ጠንቅቆ ማንበብ ያስፈልጋል።

<u>ሰንበቴ</u>

ሰንበቴ ከጽዋ ሚጎበር ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱ እንደኛ እንደ ጽዋ ሚጎበር በመር አይደለም ከሰሙ እንደምንረዳው በየሰንበቱ አሑድ አሑድ ነው፡፤ ሁለተኛ እንደ ጽዋ ሚጎበር በየቤቱ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ቅጽር ነው። ይህም ደገኛ ሥርዓት የመጣው ከሐዋርያት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ ነው። ቅዱሳን

አባቶቻችን ሐዋርያት በዘመኑ የነበሩ አባቶቻችን እያቶቻችን ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበትን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሑድ እየተሰበሰቡባት በኅብረት እንጀራን ይቆርሱ ነበር። ጌታም በመካከላቸው ይገኛ ነበር።

"በሚዕድ ተቀምጠው ሳሉ ከእሥራ አንዱ ተገለጠ" ማር ፲፮፡፲፬ (16፡14)

በሚዕድ ሳሉ እንዲህ የተገለጠላቸው እምካከ በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ በትምህርት፣ በጸሎት እያሰቡት በእንድ ካይ ይመገቡ ነበር፡፤

"ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" ሥራ ፪፡ ፵፩ (2፡41)

ይህ ሥርዓት በየሰንበቱ በሐዋርያት ይደረግ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ (፳፡፯ (20፡7) የተጻፈው ቃል ይነግረናል፡፤ "ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ከመቁረስ ተሰብሰበን ሳለን..." ይላል። ዛሬም ይህ ሥርዓት ከነበረው ሳይጎድል በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እየተፈጸመ ይገኛል።

እንባቢ ሆይ፡- የመሶበ ወርቁና የጽዋው ምሥጢር ከካይ ካለው ጋር እንድ ነው።

ይህ ሁሉ ምሥጢርና ሥርዓት ከኃያኩ እምካከ ከአግዚአብሔር ጋር እንድ ከመሆን ነው። ሐዋርያው እንደተናገረው እንዳንዶች ይህን ታላቅ የድኅነት ሥራ በመተውና በመንቀፍ ከእጋንንት ጋር ማኅበርተኛች ሆኑ ይለናል።

"ከእጋንንት ጋር ማኅበርተኛች እንድትሆኑ አልመድም። የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም ከጌታ ማዕድ ከእጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም" ፩ቆሮ፲፡፳፩ (10፡21)

ስለዚህ ይህ ቃል እንደሚነግረን በጽዋ ማኅበርም ሆነ በሰንበቱ የእግዚአብሔርን በረከቱን የምንፈልግ ምእመናን ፈጽመን ከሰይጣን ማኅበር ከክፉ ሥራውም እንርቅ ዘንድ ከእጉል እምነትም መጠበቅና መራቅ እንደሚገባ ያስተምራል። ይህ ሁሉ የጌታችንን መከራና ሞቱን ዘክሰብ በዕከተ አሑድ መነሣቱንም በመዘከርና በመናገር የዘላለምን ሕይወት እንወርስ ዘንድ ነው።

> "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለ ሆነ እኛ ብዙዎች ሰንሆን አንድ ሥጋ ነው ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።" ፩ቆሮ ፲፡፲፮-፲፰ (10፡16-18)

የጽዋ ማኅበርና ሰንበቱ ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን ምሥጢር ነው።

ኬላው ክናስተውለው የሚባ ነገር የጽዋ ማኅበርና ሰንበቱ በቅዱሳንና በመላእክት መታሰቢያ እንደሚደረግ ነው። አንዳንዱ ስው ከምን በቅዱሳን ስም ወይም በመላእክት ይደረጋል ብሎ ኪነቅፍ ይሞክራል። ሆኖም ግን በአምላክም ስም የሚደረገውም በእርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደምናየው ታላቅ ክብርን እንደሰጣቸው እንመለከታለን። የእግዚአብሔር ስምም በእነሱ ውስጥ አለ፤

> "መልአኬን በፊትህ አስዳለሁ በፊቱ ተጠንቀቅ ቃሉንም አድምጥ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠራ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።" ዘጸ ፳፫፡፳፩ (23፡21)

> "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም አስጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም አስጣቸዋለሁ።" ኢሳ ፶፮፡፭ (56፡5)

ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ቤቱ ተብሎ በተሰየመበት ሁሉና በእርሱ መታሰቢያ ከመካእከቱና ከቅዱሳን ይህንን ጸጋ ስጥቷቸዋልና በመታሰቢያ ይሰየምካቸዋል።

ሰድስቱ (፮ቱ) ቃካተ መንገሐ

አሪትና መንገሐ አንደ ጥካና አካሐ የሚይሐያዩና የሚይገነጣጠኩ ናቸው። መንገሐ ከአሪት ከነቢያት ተሐይታ መደሰው ሐቡና አትገባም። ሰሐዚሀም ነው የከብር ባሐቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ አሪትን ነቢያትን ካሳሐፉቸው የመጣሁ አይምሰካችሁ ፍጹማን ካደርጋቸው ነው አንጂ ብኩ የነገረን። በመንገሐ ማቴምስ ምዕራፍ አምስት ጌታችን አንዳስተማረን "ሰማዕከሙ ዘተብህከ ከቀደምትከሙ……." ከቀደሙ ሰዎች የተባሐውን ሰምታችኋሐ፤ "ወአነስ አብሐከሙ አኔ ግን አካችኋሐሁ አያከ ሰድስቱን ቃካተ መንገሐ ወይም ሕገ መንገሐ ዘርዝሮ ነግሮናሐ። እነሱም ከዚህ ቀጥኩ ያኩት ናቸው።

፩. መንድምህን በከንቱ አትቀጣ አታሳዝን ፭፡፳፪

፪. ወደ ሴት አይተህ በሐብህ አታመንዝር ፭፡፳፯

፫. አትፍታ ፭፡፴፪

፬. ፊጽማችሁ አትማኩ ፭፡፴፬

፭. ከፉን በከፉ አትመክሱ ፭፡፴፱

፮. ጠካታችሁን ሙደዱ ፭፡፵፭

ለድስቱ ጥያቄዎች በጊዜ ምጽአት

የክብር ባለቤት ጌታችን መድኃኒታችን ከፍርድ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንንም በግራው ያቆማቸዋል። በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። "በረከተ ገሪዛን ያደረባችሁ በረከተ ነፍስ ያላችሁ ዓለም ሳይፈጠር በጣዕም በመዓዛ በሰን በብርሃን የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ወደኔ ኑ"። በግራው ያሉትም "መርገመ ጌላክ ያደረባችሁ መርገመ ነፍስ ያለባችሁ ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ወደተዘጋጀ ወደማያልፍ ሰቃይ ሂዱ" ይላቸዋል።

ጻድቃንን "ንው ጎዜየ ቡሩካኑ ከእቡየ" የአባቴ ብሩካን ወደኔ ኑ፤ ኃጥአንን ደግሞ "ሑሩ እምኔየ ሙስተ አሳት ዘከዓለም" ወደ ዘለዓለም አሳት ከእኔ ሂዱ፤ የሚልበት ምክንያት ሁለቱን የእግዚአብሔር ንብረቶች እምነትና ምግባርን አንድ አድርገን በመያዝ ሰድስቱን ጥያቄዎች በሚገባ በመመለስና ባለመመለስ በሚመጣ ማለፍና መሙደቅ የተነሣ ነው። እነሱም በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፳፭፡፴፩-፵፮ (25:31-46) ተጽፈው እንመለከርበት ዘንድ የተገለጹት ናቸው።

፩. ከተራበ ማብላት

፪. ከተጠማ ማጠጣት

፫. እንግዳ መቀበል

፬. ከታረዘ ማልበስ

፭. የታመመ መጠየቅ

፮. የታሰረ መጠየቅ

"ብፁዕ ዘይኬቡ ካዕከ ነዳይ ወምስኪን እምዕለት እኪት ያድኅኖ እግዚአብሔር"

"ከችግረኛና ከምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል።" መዝ ፵፡፩ (40:1)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም ተብለው የተጠሩ ብዙዎች ሲኖሩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ግን የአምላክ እናት ስለሆነች ከሰው ወገን ሁሉ ልዩ ነች።

> "የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር" ሉቃ ፩፡፳፯ (1፡27)

> "ከሴቶች መካከል የተባረከሽ ነሽ" ሉቃ. ፩፡፳፰ (1፡28)

ማርያም ማለት ፀጋ መሀብት፣ ፍጽምት፣ ክዕልት፣ ተስእኪተ እግዚአብሔር መሰብእ፣ መርሕ ከመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው።

እባቷ ቅዱስ ኢያቄም ይባላል እናቷ ቅድስት ሐና ትባላለች መካን ሆነው ሲኖሩ እግዚአብሔር አምላክ በመጨረሻ ከራሱ እናት አንድትሆነው ከአባቶች ወገብ ጀምሮ ያዘጋጃትን ሴት ልጅ መሐዱ ስሟንም ማርያም ብለው ጠሯት። ወንድምም እህትም የላትም ከመካጀቷ ብቸኛ ናት።

> "ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት ከእናቷም አንዲት ናት ከመከደቻትም የተመረጠች ናት።" መሐ፡ ፮፡፱ (6፡9)

ኢያቄምና ሐና የመሐዷት በስስት ነበር። ለስታቸውም የሚመልዱትን ልጅ በቤተመቅደስ እንዲኖር ከእግዚአብሔር መሰጠት ነበር። በዚህም መሠረት ድንግል እመቤታችን የ3 ዓመት ሕፃን እንደሆነች ወደ ቤተመቅደስ አስገቧት።

> "ልጇ ሆይ ስሚ አዩ ጆሮሽንም አዘንብዩ ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን መድፈሩ እርሱ ጌታሽ ነውና" መዝ. ፵፬፡፲ (44፡10)

እመቤታችን በቤተመቅደስ 12 ዓመት ኖረች ከዚያም ለይጣን

በአይሁድ አድሮ ከቤተመቅደስ እንድትወጣ አደረጉ ምክንያታቸውም ድንግል ማርያም እንደ ሌላ ሴት መሰላቸው ነበር። እርሷ ግን ከሴቶች ሁሉ ንጽሕት ናት። ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷ ሲመጣ ያላት እንዲህ ነበር።

"ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት" ሉቃ. ፩፡፳፰ (1፡28)

ከቤተመቅደስም በወጣች ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠች ናትና ከሽማግሌዎች ከአንዱ በአደራ እንድትሰጥ ሆኖ ዮሴፍ የተባለ ቅዱስ ሰው ይጠብቃት ዘንድ ተሰጠች።

በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ የአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ በወጣች ጊዜ ዮሴፍ አመቤታችንን ይዞ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ ሄደ በዚያም አመቤታችን የዓለምን መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች። ሉቃ ፪፡፩ - ፯ (2፡1 - 7)

መካዲተ አምካከ መሆኗ

ድንግል ማርያም እመቤታችን የመከደችው ኢየሱስ እርሱ እምካከ ነው። ቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮ ነበር።

"ሕፃን ተመክዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶልናልና እለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምካከ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" ኢሳ. ፱፡፮ (9፥6)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሰማይ መርዶ ከድንግል የተመከደው የሁላችን ቤዛ ኢየሱስ እኛን ከማዳን ሰው ይሁን እንጂ እርሱ ከዘላለም የተባረከ አምካከ ነው እንዲል ሮሜ ፱፡፮ (9፥6)

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቃል በመጀመሪያ ነበር ያ ቃል እግዚአብሔር ነበረ ያም ቃል የተባለ ሥጋ ሆነ ብሎ ከድንግል ማርያም የተመከደው አምካከ እግዚአብሔር እንደሆነ ተናገረ። ዮሐ. ፩፡፩-፲፬ (1፡1-14)

ስለዚህ እመቤታችን መካዲተ አምካከ (አምካከን የመከደች) ተብላ ትጠራለች። ይህ ከሌላ ከማንም አይቀጸልም። ድንግል ማርያም ብቻ እግዚአብሔርን ልጇ ትላለች። እግዚአብሔርም ድንግል ማርያምን ብቻ እናቴ ይላታ።

"አስመ ጎረያ እግዚአብሔር ከጽዮን፡ መአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፡ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም"

"እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደርያውም ትሆን ዘንድ መጺታልና እንዲህ ብሎ ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት" መዝ፡ ፻፴፪፡፲፫ (131፡13)

መረጣት ማደሪያውም ሆነች ጸነሰችው በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሲሞላ መከደችው እቀፈችው አጠባችው ኢየሱስ አለችው አሳደገችው። እናቴ እያለ ይታዘዛት ነበር።

የጸጋና የአክብሮት ስግደትና ምስጋና ከአመቤታችን

እውነተኛ ምእመናን የእምካከ አናት ከሆነች ከድንግል ማርያም የሚገባትን ክብር ይሰጣሉ። እመቤታችን ድንግል ማርያም የባሕሚልነት፣ የመመደድ የመፈራት ልዩ ግርማ አላት። የባሕሚልነት ግርማ በሥላሴ ዘንድ የመመደድ ግርማ በመላእክትና በምእመናን ዘንድ የመፈራት ግርማ በአጋንንትና በመናፍቃን ዘንድ።

በራእይ. ፲፪፡፩-፭ (12፡1-5) "ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት በራሷ ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።" ይህች ሴት እመቤታችን ከመሆኗ ቁጥር 5 ላይ "አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች" ይላል።

ፀሐይ የተባለ - ኢየሱስ

ጨረቃ የተባሉ - ቅዱሳን

12 ከዋክብት የተባሉት - 12ቱ ሐዋርያት ናቸው ክብር ይህ ነው አጋንንት ግን ይጠሏታል።

"ዘንዶውም ወደምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።" ራእይ. ፲፪፡፲፫ (12፡13) ፀሐየ ጽድቅ አምላካችን ኢየሱስን ጸንሳ የወለደች ጨረቃ የተባሉ ቅዱሳን እነ ቅዱ ዮሐንስ መጥምቅ የሚሰግዱላት ነቢያት ትንቢታችን ሐዋርያት ሞገሳችን ሰማእታት አናታችን መላእክት አሀታችን የሚሏት ክብርት ናት።

> ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ከአመቤታች፡ን የምትሰጠው)ክብር በመጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈው መሠረት ነው። ከምሳሌ መልእክተ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷም ገብቶ እንዲህ አላት፡- "ተፈሥሒ ፍሥሕት እ ምልዕተ ፀጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምእንስት" ኩቃ. ፩፡

ጸጸ (1፥28)

አኖም ስናመሰግናት ልክ ከእግዚአብሔር እንደተካከሙ መከእከ "ደስ ይበልሽ ከሴቶች ሁሉ ልዩ የሆንሽ" እያልን እናመሰግናታለን። በመከእኩ ቅዱስ ገብርኤል ብቻ የተመለነ ምስጋና ሳይሆን ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ያመሰግናታል። ነቢያትም በትንቢታቸው ስለ እመቤታችን ሳይናገሩ አላለፉም። ቅዱስ ዳዊት በመዝ. 44 (55) ፥ 9-13 በመርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኘህ ትቆማለች። ... ከሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ከብሯ ነው።" ብሎ በእናት በአባቷ ቤት ሳይሆን በመቅደስ እንዳደገች። እግዚአብሔር ከተዋሕዶ እንደመረጣት አርሱ ደግሞ ጌታዋ እንደሆነ በቀኙ እንደምትቆም ትንግኤዋን ሳይቀር ተናገረ። መዝ. ፵፬፥፱-፲፫ (44፥9-13)

በኩቃለ ወንጌልም እንደተጻፈው ራሷ እመቤታችን ከእግዚአብሔር የተመደደ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ትሙልድ ሁሉ ከዘካለም እንደሚያመሰግናት ትናገራለች።

"ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ"

ከእንግዲህስ ወዲህ "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ኩቃ. ፩፥ ፵፰ (1፥48)

አኖም ትውልድ ነንና የመጽሐፉንም ቃል እንስማለንና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያምን ብፅዕት ብለን ምስጋና እናቀርብላታለን። ምስጋናውም የሚገለጸው በእንደበት በመመስከርና የትሕትና ምልክት የሆነውን ስግደት በመስጠት ነው። ስግደቱም የአክብሮት ስግደት ይባላል። ፀጋ ከብር ላላቸው የሚሰጥ ስግደት።

"ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማህፀኗ ውስጥ ዘለለ (ሰገደ) በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅም ጮኸ እንዲህ አለች፡- እንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።"

"ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች፡ ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ

ኤልሳቤጥን ተሳከመቻት። ኤልሳቤጥም የሚርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፤ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረከሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንደት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘለለልና።" ሉቃ. ፩፡፴፱-፵፬ (1፥39-44)

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናስተውላቸው፡

ሀ. የእመቤታችን ድምፅ ኃይል - ፅንስ ማዘለል

ለ. መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው እመቤታችንን እንደሚወዳት እንደ ኤልሳቤጥ

ሐ. ድንግል ማርያም እመቤታችን ከሰዎች (ከሴቶች) ልዩ መሆኗ

መ. ኤልሳቤጥና በማኅፀንዋ ያለው ቅዱስ ዮሐንስ ከጌታና ከድንግል መስገዳቸው

ሠ. የጌታዬ እናት ብላ ኤልሳቤጥ እመቤታችን የአምላክ እናት መሆኗን

ረ. ወደ እኔ ትመጣ ዘንደ እንዴት ይሆንልኛል ብላ ድንግል ማርያም ከብርት እንደሆነች የሚያሳይና የኤልሳቤጥ ትሕትናን በመንፈስ ቅዱስ እውቃ ሳትወልደው መናገሯ።

እንዳንዶች ከዚህ ከእግዚብሔር ቃል ውጪ በመሆን ይህንን ከብር ካለመሰጠት በትእቢትና በከሀደት ውስጥ ይታያሉ። ሰዓት አለ ሁሉም ከእመቤታችን የሚንበረከክበትና እግዚአብሔር የተመለደብሽ ከተማ ብሎ የሚያመሰግንበት።

"የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል" ኢሳ. ፷፡፲፬ (60፥14)

እንዳንድ ሰዎች ይህ የተባለው ከኢየሩሳሌም ነው፡ እንዳንዶች ደግሞ

በሊየሩሳሌም ካለ ተራራ ነው ብለው ከእመቤታችን ሰግደት አይገባም ይላሉ። እንደዚያ እንኳ ቢሆን ከእየሩሳሌምም ሆነ ከተራራው ሲሰግዱ ታይተው አያውቁም በሰሙ ከዚያ ቢነገርም ምሥጢሩ የእግዚአብሔር ከተማና ማደሪያ እመቤታችን ናት። ብናከብራት እኛ እንከብራለን እንጂ ከእሷ የምንጨምርላት ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ከዘላለም እስከ ዘለዓለም ነው። የእግዚአብሔር እናት ከመሆን በላይ በምድርም በሰማይም ምንም የለም የብርሃን እናት ብርሃናችን ድንግል ማርያም።

የእመቤታችን ቅድስናና ንጽሕና

እም ማለት በግእዝ እናት ማለት ሲሆን ብርሃን ደግሞ በብርሃንነቱ ጨለማን አስወገደ ማለት ዲያብሎስን አራቀ የተባለ ኢየሱስ ነው።

"ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።" ዮሐ. ፰፡፲፪ (8፥12)

ስለዚህ ነገር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብርሃን ነኝ ያለ የሆነ ኢየሱስን መልዳልናትና እመ ብርሃን የእግዚአብሔር ከተማ ጸዮን የብርሃን እናት ነች።

ቅድስት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሰው ሁሉ ወገን የእግዚአብሔር ከተማ ጽዮን ቅድስት ንጽሕት ናት፡፡ የእርሷ ቅድስናና የኬሎች ፈጽሞ ግንኙነት የለውም።

"እንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ" እንዲል እግዚአብሔር ስሙን በማዳን ዕቅዱ ከእርሱ ሰው መሆን ራሱ ቅድስት አድርጎ ለይቶ በአባቶች ወገብ ሲያስተካልፋት የነበረች ንጽሕት ዘር ነበረች። በዚህም ምክንያት ከጥፋት ዳንን። ኩፋ. ፭፡፵፪ (1፥42)

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር።" ኢሳ. ፩፡፲፱ (1፥19)

ስለዚህ እመቤታችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያልነካት ማለት በአዳምና በሔዋን የደረሰ ከትውልድ ሁሉ የተካለፈ ኃጢአት ፈጽሞ ያልደረሳት ቅድስት የሆነች ናት።

"ወዳጀ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው። ነውርም የለብሽም" መኃ. ፬፡ ፯ (4፡7)

ድንግል

እመቤታችን ድንግል ማርያም - ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ ማለት ጌታን ከመጽነሷ በፊት፣ በጸነሰች ጊዜ፣ ከጸነሰችም በኋላም ድንግል ናት። ልክ እንዲሁ፡- ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል ናት። ማለት ጌታችንን ከመውለዷ በፊት፣ በመውለዷ ጊዜ ከመውለዷም በኋላ ዘለዓለማዊት ድንግል ናት። ነቢዩም ይህን ድንቅ ምክንት ጌታ ይሰጣችኋል አለ።

> "ናሁ ኪያ በእንተ ዝንቱ ይሁበክሙ እግዚአብሔር ትዕምርተ፡ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ለሞ አማኑኤል"
>
> "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡" ኢሳ. ፯፡፲፬ (7፡14)

ታላቁ ምልክትና ድንቅ የሆነው ነገር ይህ ነው። እናትነትን ከድንግልና አለተባብራ የያዘች። ተአምሩም ይኸው ነው። በጎቱም ድንግልና ጌታ ከሷ ተወልዶ ሰው መሆኑን።

ነቢዩ ሕዝቅኤል የተነበየውም በዚህ ተፈጸመ እንዲህ ብሎ፡- "ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር ። እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የአሰራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።" ሕዝ. ፵፬፡፪ (44፡1)

የእመቤታችን ንጽሕናና ድንግልና በ3 ዓይነት ነው።

በጎልዮ (በሐሳብ)

በነቢብ (በመናገር)

በገቢር (በመሥራት)

በነዚህ በሦስቱም ዐይነት አመቤታችን ኃጢአት አልሠራችም። ከምላሌ ብዙ ሰዎች ድንግል ሆነው ከእግዚአብሔር ራሳቸውን ለጥተው የኖሩ አሉ። በሥጋ ድንግል ይሁኑ እንጂ በአሰተሳሰባቸው ወይም በንግግራቸው ኃጢአትን መሥራታቸው የሚይቀር ነው። አመቤታችን ግን በሐሳብም፣ በመናገርም፣ በሚድረግም ፈጽሚ ኃጢአትን ያልሠራች የእግዚአብሔር ልዩ መቅደሱ ናት።

የእመቤታችን ዕድሜ

እመቤታችን መካ ዘመንዋ በዚህ ዓለም 64 ነው።

ከተወለደችበት እስከ 3 ዓመቷ - ከ3ዓመት በእናት በእባቷ ቤት

ከ3 ዓመቷ እስከ 15 ዓመቷ - 12 ዓመት በቤተ መቅደስ

ከ15 ዓመቷ እስከ 49 ዓመቷ - 34 ዓመት በቤተ ዮሴፍና ከሐጇ ጋር

ከ49 ዓመቷ እስከ 64 ዓመቷ - ከ15 ዓመት ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር።

በ 64 ዓመቷ አረፈች ሞታ ተነስታ ዓርጋ እሁን በመንግሥተ ሰማይ ያለች የሰው ዘር እመቤታችን ብቻ ናት።